# የሐረሪ ብሔረሰብ ባህላዊ ህግ ጥናት

1. በብሔረሰቡ ግጭቶችን ለመፍታት አግልገሎት በመስጠት ላይ የሚገኙት ባህላዊ የግጭት መፍቻያ ተቋማት የሚሰጡትን አገልግሎት እና ተቀባይነት ከግምት በማስገባት የባህላዊ የፍትሕ ተቋማትን እና ሕጎችን አሰራር በተመለከተ ዝርዝር ሕግ በሕግ አውጪው አለመውጣቱ በአፈፃጸም ረገድ በርካታ ችግሮችን አስከትሏል። የህገ መንግስቱ አላማና ፍላጎትም ሙሉ በሙሉ እንዳይተገበር አድርጎታል። በመሆኑም የሕግ አውጪው አካል ጉዳዩን የሚመለከት ዝርዝር ሕግ በማውጣት ይህን ችግር ሊፈታው ይገባዋል። የሐረሪ ብሔረሰብ ማሕበራዊ፣ ባህላዊ እና ሐይማኖታዊ ተቋማት፡- - በተለያዩ ብሔረሰቦች እና ሐይማኖት ተከታዮች መካከል የሚነሱ ግጭቶችን፣ - በግድያ ምክንያት የሚከሰቱ ቅራኔዎችን፣ - በቤተሰብና በውርስ ጉዳዮች የሚነሱ አለመግባባቶችን - በድንበር፣ በመሬት አጠቃቀም፣ በጋራ የግጦሽ፣ የውኃ እና መሰል የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም እና የይገባኛል ጥያቄ ዙሪያ የሚነሱ አለመግባባቶችን ለዘለቄታው እና ውጤታማ በሆነ መንገድ በመፍታት ረገድ ውጤታማ ናቸው። በመሆኑም ስራቸውን የበለጠለ ማቀላጥፍ የሚችል ዝርዝር ሕግ ሊወጣ ይገባል።

2. ከዚህ በፊትም ሆነ ወደ ፊት በባህላዊ ህግ ዙሪያ ለተደረጉ እና ለሚደረጉ ጥናቶች የሚመለከታቸው አካላት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል። በተለይ በዚህ በኩል የትኞቹ የባህላዊ ሕጎች እና ቷቋማት ናቸው ጠቃሚዎቹ? ሕገ መንግሥቱ ካስቀመጣቸው መሰረታዊ መርሆዎች ጋር ተጣጥመው መሄድ የሚችሉት እንዴት ነው? ባህላዊው ሕግና መደበኛው የሕግ እና የፍትህ ሥርዓት እንዴት ሊመጋገቡ ይችላሉ? ወዘተ... የሚሉትን በስፋት መርምሮ ጠቃሚ የሚባሉትን ለይቶ ለማወቅ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። ከአካባቢ ባህላዊ የግጭት መፍቺያ ተቋማት ውስጥ ግጭቶቸን በመፍታት የጎላ ልምድ ያላቸውን የሀገር ሽማግሌዎች በመምረጥ የህግ፣ የፖለቲካ ሳይንስ የታሪክ፣ የአንትሮፖሎጂ፣ የስነ ህዝብ ወዘተ ምሁራንን ያቀፈ ውይይት እና አገር አቀፍ ኮንፈረንስ በማዘጋጀት ብሄረሰቡ አንድ ወጥ በሆነ መልኩ ግጭትን የሚፈታበት፣ የማህበረሰቡን የፍትህ አመለካከት እና

አተያይ መሰረት ያደረገ ዘመናዊ የግጭት መከላከያ እና መፍቻ ደንብ ከሀገሪቷ እና አለም አቀፋዊ ሁኔታ ጋር እየተገናዘበ በፖሊሲ ደረጃ የሚቀረጽበት ስልት መቀየስ እና ይህንንም ገቢራዊ የሚያደረግ ተቋም የሚቋቋምበትን መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ በሐረሪ የተቋቋሙት የሀገር ሽማግሌዎች ጉባዔ እና የሐይማኖት አባቶች ምክር ቤት አርአያ ሊሆን የሚችል ትልቅ ተግባር እያከናወኑ መሆኑን ለመረዳት ችሏል። በመሆኑም ይህ አይነቱ ጥረት በሌሎች ክልሎችና በሀገር አቀፍ ደረጃ ሊተገበሩ እና ድጋፍ ሊሰጣቸው ይገባል።

3. ግጭቶችን አስቀድሞ የመከላከል እና ሲከቱም በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ባህል ውጤታማ እና ቀልጣፋ የሚሆነው የህዝብ ተሳትፎ ሲኖር ነው። የማህበረሰቡ ወይም የህዝቡ ተሣትፎ መኖር የሐረሪ ብሔረሰብ ባህላዊ እና ማሕበራዊ ተቋማት ዓይነተኛ መገለጫ እንደመሆኑ መጠን በየደረጃው ያሉ የፖለቲካው ስርአትና የመደበኛው የፍትህ አካላት ግጭቶችን እንዴት መከላከል እና መቆጣጠር ብሎም መፍታት እንደሚቻል በግጭት ፈቺነት ከሚሰተፉት የሃገር ሽማግሌዎች ምክር የሚያገኙበትን አደረጃጀት፣ መዋቅርእና አሰራር መፍጠር ያስፈልጋል።

4. እያንዳንዱ ግጭት የራሱ ባህርይና መንስኤ እንዳለው በመረዳት ከግጭቱ ዓይነትና ከህዝቡ ባህል አንፃር እየታየ ከአካባቢው ባህላዊ ግጭት መፍቻ ተቋማት ጋር በህብረት በመስራት ግጭቶችን የመፍታት ልምድ ይበልጥ የሚዳብርበትን ሁኔታ መፍጠር እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች እና ከምንጊዜም በላይ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።